Venture Meda

Job Creation through Incubation and Acceleration Support in Ethiopia

## ቬንቸር ሜዳ: በኢንኩቤሽን እና በአክስለሬሽን ድጋፍ የስራ ፈጠራ በኢትዮጵያ

# ደንቦች እና መመሪያዎች

### 1. የህትመት ወይም የማስታወቂያ ስራዎች

የቬንቸር ሜዳ ፕሮግራም አጋሮች የእጩ አመልካቾችን፣ ወይም በመጨረሻ ዙር ያለፉትን ተወዳዳሪዎች ማንነት እና ዝርዝር መረጃዎች በድርጅቶቻቸው ድህረ ገፆች እና በሌሎች አስፈላጊ ነው ብለው በሚያስቧቸው የህዝብ ግንኙነት ሚዲያዎች ላይ የማሳተም መብታቸው የተጠቀበ ነው።የፕሮግራሙ ተሳታፊዎች በፕሮግራሙ ላይ ሲሳተፉ በህዝብ ግንኙነት ሚዲያዎች፣ በማስታወቂያዎች እና/ወይም በፕሬስ ኮንፈረንሶች ላይ ለመሳተፍ እንዲሁም የፕሮግራሙ አዘጋጆች የተሳታፊዎችን ስም፣ ፎቶግራፍ እና ሌሎች ለህዝብ ግንኙነት ተግባራት የሚውሉ መረጃዎችን በማንኛውም ሚዲያ ከክፍያ ነፃ በሆነ መልኩ እንዲያስተላልፉ ተስማምተዋል ማለት ነው።

### 2. ህጋዊነት

በአክስለሬተር ፕሮግራሙ ለመሳተፍ ከክፍያ ነፃ ሲሆን፣ ማንኛውም ችግር ፈቺ እና ለውጥ አምጭ የሆኑ የፈጠራ ሃሳብ ያላቸው፣ የኤሌክትሮኒክ ንግድ ተቋማት ማመልከት ይችላሉ። ተቋማዊ አደረጃጀት ያላቸው፣ በኢትዮጵያ ውስጥ ለሚገኙ ስራ-ፈጣሪዎች በሙሉ ክፍት ነው። የሚያመለክቱት ቡድኖች ወይም ኩባንያዎች የሚከተሉትን መስፈርቶች ማሟላት አለባቸው፡

- የኢትዮጵያ ነዋሪ የሆኑ
- የመስራቾቹ እድሜ ቢያንስ 18 አመት ቢበዛ 35 አመት የሆኑ
- ቢያንስ 2 አባላት ያሉት ተቋም
- ቢያንስ ለስድስት ወር ገቢ ማግኘት የቻሉ (Post-revenue) (ከስድስቱ ወር ዉስጥ ቢያንስ ለሶስት ወራት ትርፋማ የሆኑ)

የኢኖቬሽንና ቴክኖሎጂ ሚኒስቴ

iceaddis

mastercard foundation

- አስቀድሞ በገበያ ላይ ያለ የኢ-ኮሜርስ ምርት ወይም አገልግሎት ያላቸው።
- ተገቢውን ቴክኖሎጂን መምረጥ እና መተግበር (የቴክኒክ አዋጭነት)።
- ወደ እድገት እና ዘላቂነት የሚያደርሰውን ገቢ በማግኘት የንግዱን የዕድገት አቅም ማሳየት የሚችሉ
- ለሶስተኛ ወገን ንግዶች (ቢያንስ 18 ስራዎች በዓመት) የስራ እድሎችን እና ገበያዎችን ለመፍጠር ቁርጠኛ የሁኑ።

ሴት ስራ ፈጣሪዎች እንዲሁም ሴት መር የሆኑ ኩባንያዎች፣ በአካል ጉዳተኞች፣ በሀገር ውስጥ ተፈናቃዮች ፣ በስደተኞች ወዘተ የሚመሩ ተቋማት/ነግዶች በዚህ የአክስለሬሽን ፕሮግራም ላይ ተሳትፎ እንዲያደርጉ በከፍተኛ ሁኔታ ይበረታታሉ። ከላይ የተጠቀሱት ብቻ ሳይሆኑ ሌሎችም እንደ አመልካቾቹ ሁኔታ ከህጋዊነት መስፈርቶች ጋር የተገናኙ ጥያቄዎች ሁልጊዜም ከግምት ዉሰጥ ይገባሉ።

በተጨማሪም ፕሮግራሙ ወጣት ወንዶች እና ሴቶችን ተጠቃሚ እንደሚያደርግ ለመወሰን የሚከተሉትን ኹቶች ከግምት እናስገባለን።

## 3. ትርጓሜዎች

ውድድሩ በተለያየ አይነት የኤሌክትሮኒክ ንግድ በተለይ በግብርና፣ በማኑፋክቸሪንግ፣ በመዓድን እንዲሁም ተያያዥ በሆኑ ኢንደስትሪዎች፣ አይሲቲ እና የፈጠራ ጥበብ፣ ቱሪዝም እና ተያያዥ ዘርፎች እንዲሁም በእሴት ሰንሰለቶች ላይ ላተኮሩ ሁሉም አካላት ክፍት ነው። የኤሌክትሮኒክ ንግድ ስታርታፖች፤ ለተጠቃሚዎች የሚደርስ ንግድ ስራ (ቢ2ሲ) ፣ ንግድ ለንግድ(ቢ2ቢ) ፣ ከሸማቾች ወደ ንግድ ስራ (ሲ2ቢ) ፣ ከሸማቾች ወደ ሸማቾች (ሲ2ሲ) ወዘተ፤ ፊንቴክ ስታርታፖ (የሞባይል ክፍያዎች፣ ክራውድ ፈንዲንግ ፕላትፎርሞች፣ ብድር፣ ኢንሹራንስ ወዘተ እና ሎጂስቲክስ (አገልግሎት፣ የአቅርቦት ሰንሰለት፣ አቀናባሪዎች፣ የደንበኛ አያያዝ ማከማቻዎች ወዘተ) ያካትታል።

## 4. ማመልከቻ አቀራረብ

Venture Meda

Job Creation through Incubation and Acceleration Support in Ethiopia

ለቬንቸር ሜዳ አክስለሬሽን 2014/15 ፕሮግራም ማመልከቻ ማስገቢያ የመጨረሻው ቀን ገዶብ ታህሳስ 11 2015 ዓ.ም ነው።

አመልካቾች ማመልከቻቸውን ማስገባት ያለባቸው በተያያዥ ኦንላይን ቅፆች (እባክዎ https://venturemeda.com/apply ይጎብኙ) ላይ ብቻ ነው።

አመልካቾች በማመልከቻ ቅፁ ላይ ማቅረብ ያለባቸው ዝርዝር ማብራሪያዎች፡

- የፈቷቸውን ችግሮች፣ የቢዝነስ ሞዴሎች እና የእሴት ሁኔታ (value proposition)
- ደንበኞችዎ አይነት፣ በሚሰጡት አገልግሎት ማን ተጠቃሚ ይሆናል
- አሁን ያሉበት የንግድ ደረጃ (እስከአሁን ድረስ ያሉ የስኬት ታሪኮች፣ ለውጦች፣ ቁልፍ ምእራፎች)
- አሁን ያሉብዎት ተግዳሮቶች እና
- የሚያስፈልግዎት የድጋፍ አይነት
- መያያዝ ያለባቸው ሰነዶች፡-
    - የተሟላ አዋጭ የንግድ እቅድ (ፒች) (ማለትም የንግድ ዕቅዱ በገበያው ውስጥ ያለውን ችግር ለመፍታት ግልጽ ዓላማ ያለው እና ደንበኞችን የመለካት አቅም ያለው መሆን አለበት።)
    - የታደሰ የንግድ ፍቃድ

የመረጃ መስፈርቶች፡-

- ኢንቨስትመንት
- የስራ እድል ፈጠራ
- ወደ ውጭ የመላክ አቅም ያላቸው ምርቶች(Export)
- ነባር ኢ-ኮሜርስ
- የታቀደው መፍትሄ/ምርት ፈጠራ ገጽታዎች
- አዋጭነት/አዋጭ የንግድ ሞዴል
- የተጨመረ እሴት
- የማደግ አቅም

MInT
የኢኖቬሽንና ቴክኖሎጂ ሚኒስቴ

iceaddis

mastercard foundation

- የቡድን አባላት/መስራች/ቾች ያላቸው ተጨማሪ ችሎታ/ዎች

በመጀመሪያ ዙር የተመረጡ እጩ አመልካቾች ተጨማሪ ዝርዝር ማመልከቻ እንዲያስገቡ ይጠየቃሉ። እንዲሁም ለመጨረሻ ዙር ያለፉ አመልካቾች የቃለ መጠይቅ /ፒች ይጠራሉ። በዚህም ዙር የመጀመሪያው ባች ተሳታፊ ስታርታፖች ዝርዝር ይወሰናል።

የአመልካቾች ውጤት በታህሳስ ወር 2015 ዓ.ም አጋማሽ ላይ ይገለፃል። የተመረጡ የስታርታፖች በአይስአዲስ አክስለሬሽን ፕሮግራም መዋቅር፣ ከኢንዱስትሪ መሪዎች ጋር የመማር እድል ፣በንግድ ስራ ባለሙያዎች ስልጠና እንዲሁም የመነሻ የገንዘብ ድጋፍ የማግኘት እድል ይኖራቸዋል።

### 4.1 የማመልከቻ ማስገቢያ ቋንቋ

ተሳታፊዎች ማመልከቻዎቻቸውን በአማርኛ ወይም በእንግሊዘኛ ቋንቋ ማስገባት ይችላሉ።

### 4.2 ልዩ ልዩ ድንጋጌዎች

አመልካቾች የእነዚህን ፕሮግራም መስፈርት ማሟላታቸዉን ለውሳኔ ሰጪው አካል ከመቅረባቸው በፊት ይረጋገጣል።

በኔትዎረክ ችግር ምክንያት ለዘገየ ማመልከቻ የፕሮግራም አዘጋጆች እንዲሁም አጋሮች ኃላፊነት የለባቸውም።

## 5. የመረጣ ኮሚቴ እና ውሳኔ ሰጪው አካል

መረጣው የሚከናወነው በሚከተሉት መስፈርቶች ነው፡

- ድርጅቶች በምርጫ ኮሚቴው ከተጣሩ በኋላ፣ እንዲፀድቁ ወደ ዳኞች ይተላለፋሉ።
- የመጨረሻ ተወዳዳሪዎቹ በጥብቅ የዳኝነት መስፈርት ተገምግመው ይመረጣሉ።

- የምርጫ ኮሚቴውእንደ አስፈላጊነቱ፣ ስለ ማመልከቻዎቹ ኦርጅናልነት እንዲሁም የተጭበረበረ እና የሌሎች ሶስተኛ ወገኖችን የአእምሮ ፈጠራ ሀብት አለአግባብ የተጠቀሙ መሆኑን ከገመተ፣ ተገቢ የሆነ የሶስተኛ ወገን ባለሙያዎችን ምክር እና ማጣራት የመጠየቅ መብቱ የተጠበቀ ነው።
- የምርጫ ኮሚቴው አባላት እና ዳኞቹ

  ሀ. የግል የገንዘብ ጥቅም ተጠቃሚነት ወይም ፍላጎት ያላቸው ወይም ሰራተኛ፣ ኦፊሰር፣ ዳይሬክተር፣ ወይም የማንኛውም በተሳታፊነት የተመዘገበው ተቋም አባል ከሆኑ፣ ኮሚቴውን ማሳወቅ አለባቸው።

  ለ. ተሳታፊ ሆኖ በተመዘገበው ወይም የተሳታፊው ስፖንሰር ከሆነ ተቋም ጋር የፋይናንስ ግንኙነት ያላቸው መሆናቸውን በተለይ እነዚህ አባላት ማመልከቻዎቹን የሚገመግሙ፣ የሚፈትሹ ወይም ከተያያዥ ተሳታፊዎች ድምፅ የሚሰጡ ከሆነ ይህንን ማሳወቅ አለባቸው።
- የዳኞች ውይይት ተሰንዶ ይቀመጣል። ውሳኔው በዳኞቹ የድምፅ ብልጫ የሚወሰን ይሆናል። የዳኞቹ ውሳኔ በገለልተኝነት የሚሰጥ፣ ገዢ እና ጥያቄ የማይቀርበት ነው። ዳኞች አሸናፊ የማወጅ ወይም ማንኛውንም ሽልማት የማስረከብ ግዴታ የለባቸዉም። ከላይ እንደተገለፀው የዳኞቹ ውሳኔ የመጨረሻ እና ይግባኝ የማይቀርብበት ነው።

## 6. እርዳታ እና ድጋፍ

በቬንቸር ሜዳ አክስለሬተር ለተመረጡ ስታርታፖች የጥሬ ገንዘብ ድጋፍ ይኖራቸዋል። ሆኖም ኮሚቴው በራሱ ፍላጎት ከፋፍሎ ሊሰጥ ይችላል። በማንኛውም ሁኔታ ይህ የተከፋፈለው ሽልማት በተቀመጠለት መርሃ ግብር ይሰጣል።

ጠቅላላ ለክፍፍል የቀረበው 50,000 ዩኤስዲ የሚደርስ ድጋፍ ለ10 ስታርታፖች የሚካፈል ይሆናል።የገንዘብ ድጋፉ የአክስለሬሽን ፕሮግራም አካል ሲሆን በተጨማሪም ፕሮፌሽናል የንግድ ስራ ማማከር እና የንግድ ስራ እንዲሁም የገበያ ትስስር እድሎችን ያካትታል።

የገንዘብ ድጋፎች/ሽልማቶች የሚሰጡት በአጋሮቹ ቁጥጥር በሚደረግባቸው ቅፆች በተገለፀው መሰረት ነው። ሆኖም እነዚህ የገንዘብ ድጋፎች/ሽልማቶች ለሌላ አካል የሚሰጡ ወይም ሊወጡ የሚችሉ አይደሉም። የገንዘብ

ድጋፉ/ሽልማቱ በአሸናፊው አማካኝነት የሚከፈሉ ዊዝልዲንግ ታክስ (ተፈፃሚ ከሆነ) እና/ወይም የገቢ ግብር እና ሌሎች ተፈፃሚ የሆኑ ግብሮች ካሉ የሚቀነሱበት ይሆናል። አጋሮቹ ከሽልማቱ ላይ ለሚከፈለው ግብር ምንም አይነት ኃላፊነት የለባቸውም።

የቀረበው ማመልከቻ ወይም መስፈርቶቹ የተጭበረበሩ መሆናቸው በሂደት ከተለየ የተሰጠው ሽልማት ሊመለስ ይችላል።

## 7. መብቶች እና ግዴታዎች

### 7.1 የአዘጋጆቹ

አጋሮቹ የቀረቡትን ማመልከቻዎች እና ፕሮጀክቶች በከፍተኛ ሙያዊ ሃላፊነት እና ጥንቃቄ ይገመግማሉ። አጋሮቹ ስለ ተሳታፊዎቹ ማንነት ውጤቶቹ በይፋ ከመውጣቱ በፊት ለሚቀርቡላቸው ጥያቄዎች ምላሽ መስጠት አይኖርባቸውም።

ማንናውም ግላዊ መረጃዎች በሚስጥር ይያዛሉ።

ከዳኞች ውሳኔ በኋላ አጋሮቹ የማመልከቻውን ምስሎች ሊጠቀሙ፣ ስለ ተሳታፊዎቹ መረጃዎችን ሊሰጡ እንዲሁም በፕሮጀክት ፈጣሪው የተመዘገቡትን ስሞች ሊጠቀሙ ይችላሉ። አጋሮች ከአቅም በላይ በሆነ ምክንያት ለተለወጠ፣ ለተበላሸ፣ ለዘገየ፣ ወይም ለተሰረዘ ማመልከቻ ሃላፊነት የለባቸውም።

### 7.2 ተሳታፊዎች

የቬንቸር ሜዳ የአክስለሬሽን 2014/15 ፕሮግራም ተሳታፊዎች በዚህ ሰነዶች የተገለፁትን ግዴታዎች እንዲሁም ውጤቶች ያለ ምንም ይግባኝ ለመቀበል ተስማምተዋል።

ተሳታፊዎች ባቀረቧቸው ማመልከቻዎች ላይ ያሉትን የአእምሮ ሃብት ፈጠራዎች የራሳቸው መብቶች ናቸው። በክፍል 7.1 ላይ የተገለፀው የማሳተም መብት በዚህ ላይ ተፅዕኖ አይፈጥርም። በማመልከቻቸው ላይ የእነዚህ ፕሮጀክቶች ዋና

Job Creation through Incubation and Acceleration Support in Ethiopia

ፈጣሪ መሆናቸውን እንዲሁም የሀሳቡ ባለቤት መሆናቸውን መግለፅ ያለባቸው ሲሆን በተጨማሪም ሶስተኛ ወገንን የሚከለክሉ የህግ ድንጋጌዎችን በግልፅ ማካተት ይኖርባቸዋል።

**8.** የተጨማሪ መረጃዎች

አይስአዲስ የሚቀርቡለትን ጥያቄዎች በ apply@iceaddis.com ይመልሳል።